COMMENT

# Adopted Child's Right of Inheritance from the Family of Origin

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v15i2.8

Wondewosen Ewunie ♣


## Abstract

The relationship between adopted child and his/her family of adoption and family of origin is regulated under the Revised Family Code Proclamation No. 213/2000. Accordingly, the adopted child shall retain his/her bond with the family of origin in addition to his/her close relationship with the family of adoption by considering him/her, for all purposes, as the child of the adopter. One of the issues that arises in connection with a child's relationship with his/her family of origin and family of adoption is the right to inheritance. In particular, the issue arises whether the adopted child can inherit his/her family of origin (through intestate succession) while s/he is deemed to be the child of the adopter and bestowed with all rights and duties including inheritance. The assurance of inheritance right to the adopted child from the estate of his/her family of origin depends upon how much the bond with his/her family of origin is maintained. This article focuses on the legal regime with regard to the adopted child's relationship with his/her family of origin with particular emphasis on the adopted child's right to inherit his/her family of origin, in Ethiopia.



## Key terms

Inheritance right · Adopted child · Adoptive parents · Natural parents

**Suggested citation**:

Wondewosen Ewunie (2021), 'Adopted Child's Right of Inheritance from the Family of Origin' (in Amharic), 15 *Mizan Law Review* 2: 543-556

ወንደወሰን እውኔ (2014 ዓ.ም)፣ 'የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት በኢትዮጵያ ሕግ'፣ ሚዛን የሕግ መጽሔት፣ ቅጽ 15 ቁጥር 2፣ ገጽ 543-556


---

♣ Wondewosen Ewunie, LL.B, LL.M (in Business Law) Addis Ababa University, Prosecutor at Ministry of Justice.
Email: ewuniewondewosen@gmail.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0001-9004-0222

# የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት በኢትዮጵያ ሕግ

ወንደወሰን እውኔ♣

## አህፅሮተ ይዘት (Abstract)

በጉዲፈቻ ልጅ እና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ እና በቀደምት ቤተሰቦቹ መካከል እንዲኖር የተፈለገው ግንኙነት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ተደንጓል፡፡ በዚሁ መሠረት የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጅ ተቆጥሮ ከእነርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው ቢደረግም ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ያለው ግንኙነትም ተጠብቆ እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ እና ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ከሚኖረው ግንኙነት ጋር በተያያዘ ከሚነሱት ጉዳዮች መካከል የውርስ መብት አንዱ ነው፡፡ በተለይም የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጅ ተቆጥሮ መብቶች እና ግደታዎች ሁሉ የተሰጡት ሆኖ ሳለ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን ሊወርስ ይችላል ወይ የሚለው ነጥብ ክርክር ሊደረግበት ይችላል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት የተጠበቀ መሆን አለመሆኑ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በተጠበቀበት መጠን ልክ ይወሰናል፡፡ ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በሚገዛው የሕግ ድንጋጌ ላይ አትኩሮቱን ያደረገ ሲሆን፣ በተለይም የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት ያለው መሆን አለመሆኑን ይመለከታል፡፡

## ቁልፍ ቃላት፡-

የውርስ መብት፣ የጉዲፈቻ ልጅ፣ የጉዲፈቻ ቤተሰብ፣ የተፈጥሮ ቤተሰብ

---

## ይዘት

አህፅሮተ ይዘት

1. መግቢያ

2. የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ትስስር

   2.1 የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

   2.2 የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

3. የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የመውረስ መብት

4. መደምደሚያ

የተጠቀሱ ጽሑፎች

---

♣ ወንደወሰን እውኔ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም (በቢዝነስ ሕግ)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር ዐቃቤ ሕግ
ኢሜይል ewuniewondewosen@gmail.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0001-9004-0222

## 1. መግቢያ

በጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈጠር ዝምድና በጉዲፈቻ ልጅ፣ በጉዲፈቻ አድራጊው እና በጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ወላጆች መብትና ግደታዎች ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡[1] የጉዲፈቻ ስምምነቱ በእነዚህ አካላት መብቶችና ግደታዎች ላይ የሚኖረው የተጽእኖ ዓይነት እና መጠንም በሕግ የሚወሰን ነው፡፡ በጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈጠር ዝምድና ተጽእኖ ከሚያሳድርባቸው መብቶች መካከል አንዱ ያለኑዛዜ የሞተን ሰው የውርስ ሀብት የመውረስ መብት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይም በጉዲፈቻ ስምምነት ዝምድና ሲፈጠር የጉዲፈቻ ልጅ የጉዲፈቻ አድራጊውን እና/ወይም የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ላይ ተፅእኖ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ ከዚህ አኳያ በጉዲፈቻ ስምምነት ላይ ሕጉ የሚያደርገው ቁጥጥር ሲገመገም ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ የሚነሳው ክርክር ነው፡፡[2] በዚህም የጉዲፈቻ ልጅ እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ተቆጥሮ የጉዲፈቻ አድራጊውን የውርስ ሀብት እንዲወርስ መብት ከተሰጠው በኋላ በድጋሚ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት ሊወርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው የክርክሩ ዋነኛ ማጠንጠኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ የፌደራል የተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ (ከዚህ በኋላ የተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ እየተባለ የሚጠቀስ) የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ስለሚቆጠር[3] የጉዲፈቻ አዲራጊውን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ያለው ስለመሆኑ አከራካሪ አይሆንም፡፡ በአንፃሩ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው የዝምድና ግንኙነት ተጠብቆ እንደሚቆይ ቢደነገግም[4] በጉዲፈቻ ልጅ እና በተፈጥሮ ቤተሰቦቹ መካከል ተጠብቆ የሚቆየው ግንኙነት ዓይነትና ይዘት በግልፅ ባለመደንገጉ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ክርክር ሲነሳበት ይስተዋላል፡፡ ጸሐፊውም በሥራው አጋጣሚ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት ተካፋይ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ በሙያ አጋሮቹ መካከል በልዩነት ክርክር ሲደረግበት አስተውሏል፡፡

ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በጉዲፈቻ ወደ ውጭ ሀገር ሄዳ ያደገች ግለሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የተፈጥሮ ወላጆቿ በሕይወት ሳሉ ያፈሩት ቤት በውርስ ለእኔ ይገባኛል በማለት ቤቱን ይዘው ሲጠቀሙበትና ሲያስተዳድሩት በነበሩ ግለሰቦች ላይ በፍ/ቤት የክስ አቤቱታ በማቅረቧ ነው፡፡ ክሱ የቀረበባቸው ንብረቱን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ሰዎች የሕግ አገልግሎት ድጋፍ ለማግኘት ጉዳዩን ጸሐፊው በሚሠራበት ተቋም የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ለሚከታተል ባለሙያ አቅርበው የጉዲፈቻ ልጅቷ የሟች የተፈጥሮ ወላጆቿን የውርስ ሀብት ልትወርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጉዳይ በሕግ ባለሙያዎች መካከል በልዩነት ክርክር ተደርጎበታል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅቷ የሟች የተፈጥሮ ወላጆቿን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ላይ ይህ ክርክር መነሳቱ በጉዲፈቻ ልጅ እና በተፈጥሮ ወላጆች መካከል ተጠብቆ የሚቆየው የዝምድና ግንኙነት ዓይነት እና ይዘት

---

[1] Paul A Kiefer (1966), 'Intestate Succession, Sociology and the Adopted Child' 11(2) *Vill L Rev* 392

[2] Donald E Bjertness (1957), 'Domestic Relations - Inheritance by Adopted Children - Right of Adopted Child to Inherit from Its Natural Parent' 33(2) *N.D. L. Rev.* 241፣ 243

[3] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 213፣ 1992፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ 6ኛ ዓመት፣ ቁ.1፣ አንቀጽ 181

[4] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 183(1)

እስከምን ድረስ እንደሆነ በተለይም የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብትን ስለማካተት አለማካተቱ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ስለመሆኑ አመላካች ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዓላማም በጉዲፈቻ ልጅ እና በተፈጥሮ ቤተሰቦቹ/ቿ መካከል ያለው በሕግ ጥበቃ የተደረገለት ትስስር እስከምን ድረስ እንደሆነ መመርመር ነው፡፡ በተለይም የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት እና በተቃራኒ የሚነሱ ክርክሮችን በሚመለከት አግባብነት ካላቸው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች እና ተያያዥነት ካለው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር በመመርመር በሕጉ አተረጓጎም ረገድ የተሻለ ግልጽነትን መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት ተጠብቆ መቆየቱ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን በመውረስ መብቱ ላይ የሚኖረው አንደምታ እንደሚከተለው ይብራራል፡፡

## 2. የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ትስስር

በጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈጠር ዝምድናን የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅም የበለጠ የሚያስጠብቅ እንዲሆን ለማድረግ ሀገራት የሕግ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡[5] በአንዳንድ ሀገራት ሕግጋት የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅም ለማሳደግ በሚደረግ ጥረት ልጅየው ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት (የመውረስ መብቱን ጭምር የሚያሳጣ እስኪሆን ድረስ) ሙሉ ለሙሉ እንዲቋረጥ የሚያደርጉ ሕግጋቶች ይወጣሉ፡፡[6] በሌላ አነጋገር የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ፍፁማዊ የልጅነት ትስስር እንዲኖረውና ከቀድሞ የተፈጥሮ ቤተሰቡ ጋር የነበረው ግንኙነት ጨርሶ እንዲቋረጥ ይደረጋል ማለት ነው፡፡ ይህም የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንደፀና የጉዲፈቻ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ የሚኖሩት ሁሉም መብቶች እና ግዴታዎች ቀሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ዓይነት አሠራር የጉዲፈቻ ልጅ ፍፁም እንደጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ልጅ ተቆጥሮ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ የሚኖሩት መብቶች እና ግዴታዎች ሙሉ ለሙሉ ወደ ጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ እንዲዛወር ያደርጋል፡፡

በአንፃሩ እንደ ስፔን ያሉ ሌሎች ሀገራት የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅም የበለጠ ያስጠብቃል ብለው የሚያስቡትን መነሻ በማድረግ፣ የጉዲፈቻ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ማናቸውም ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ቅርብና ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስር ለመፍጠር ዕድል የሚሰጡ ሕግጋትን ይጠቀማሉ፡፡[7] ይህ ዓይነቱ አካሄድ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ቅርብና ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖረው ከማድረግም ባለፈ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘም የሚኖሩት መብቶች እና ግዴታዎች እንደተጠበቁ የሚቆዩበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡ ይህም ከፊል የልጅነት ትስስርን የሚፈጥር የሕግ ሂደት ወይም አሠራር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

---

[5] Paul A Kiefer, *Supra* note 1 pp. 393-394

[6] John R Jr Murphy (1957), 'Adopted Child's Right of Inheritance from the Natural Parents' 6 *Clev-Marshall L Rev* 148

[7] Arthur R Thompson (1917), 'Right of the Adopted Child in Intestate Succession' 3(2) *ABA J* 135

በኢትዮጵያም በጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈጠር ዝምድና የጉዲፈቻ ልጅየውን መልካም አስተዳደግና ጥቅምን የሚያረጋግጥ እንዲሆን የሕግ ቁጥጥር ተደርጎበታል፡፡[8] የሕግ ቁጥጥሩም ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍ/ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ እንዳለበት ከሚገልፀው አስገዳጅ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ይጀምራል፡፡[9]

ሕፃናትን በሚመለከት ከሚወሰዱ እርምጃዎች መካከል አንዱ ሕፃናቱ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን የሕግ ሥርዓት መዘርጋት እና ቁጥጥር ማድረግ ነው፡፡ በዚህ የጉዲፈቻ ሥርዓት መዘርጋት እና ቁጥጥር ሂደት ውስጥ የሕግ ቁጥጥር ከሚደረግባቸው ሁኔታዎች መካከል ደግሞ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት አንዱ ነው፡፡ በሀገራችን የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነትን ጨምሮ የፌደራል የጉዲፈቻ ሥርዓት የሚገዛው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሲሆን ሥርዓቱ እና ቁጥጥሩም ለሕፃናቱ ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት መልካም አስተዳደጋቸውንና ጥቅማቸውን የሚያረጋግጥ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አኳያ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅ እንደጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ልጅ ከተቆጠረ በኋላ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹም ጋር የነበረው የዝምድና ትስስር እንዲቀጥል ስላደረገ የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ከፊል የልጅነት ትስስርን የሚፈጥር አካሄድን የሚከተል እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ መሠረት የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ትስስር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የተቃኘበትን አግባብ ከጉዲፈቻ ልጅየው የውርስ መብት አንፃር በማገናዘብ እንደሚከተለው ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

## 2.1 የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ በሕግ በመደንገግ ቁጥጥር ማድረግ የጉዲፈቻ ልጁን ጥቅም ከማስከበር አንፃር የላቀ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ አኳያ (ከላይ እንደተመለከተው) በአንዳንድ ሀገራት የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅም የበለጠ ያስጠብቅለታል ተብሎ የታሰበውን ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረውን ትስስር ሙሉ ለሙሉ የሚያቋርጥ እና ከጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ጋር ጠንካራና ሙሉ ትስስር እንዲኖረው የሚያደርግ ሕግና ሥርዓት በመዘርጋት ፍፁም የልጅነት ትስሰር የጉዲፈቻ ሥርዓትን ይከተላሉ፡፡ በአንፃሩ ሌሎች ሀገራት የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ትስስር እንደተጠበቀ ሆኖ ከጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲኖረው የሚያደርግ ሕግና ሥርዓት በመዘርጋት ከፊል የልጅነት ትስስር የጉዲፈቻ ሥርዓትን ይከተላሉ፡፡

በኢትዮጵያ፣ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(2) ድንጋጌ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሕገ መንግሥታዊ ግደታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሕግ አውጭው የመንግሥት አካል ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች ለሕፃናቱ ደህንነት ቅድሚያ የሰጡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሕገ መንግሥታዊ ግደታ አለበት፡፡ ሕግ አውጭው ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች ለሕፃናቱ ደህንነት ቅድሚያ የሰጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ ረገድ ሊያከናውን ከሚችላቸው ተግባራት መካከል አንዱ የጉዲፈቻ የሕግ ሥርዓትን

[8] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 194/2

[9] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁ. 1፣ አንቀጽ 36(2)

መዘርጋትና ቁጥጥር ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ሕግ አውጭው ጉዲፈቻን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ፣ ቀድሞውንም በሀገራችን የነበረ እና በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በተለያየ ስያሜ ይታወቅ የነበረው[10] (በጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈጠር) የልጅ እና የአባት/የእናት ግንኙነት የሕግ ሥርዓት እንዲዘረጋለት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት አድርጓል፡፡[11]

በዚሁ መሠረት የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ቤተሰባዊ ትስስር እንደተጠበቀ ሆኖ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ተደርጎ እንዲቆጠር የሚያስገድድ ድንጋጌ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም በጉዲፈቻ ልጅ እና በጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ መካከል ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲፈጠር በማድረግ የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅም የበለጠ የሚያስጠብቅ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡

የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ እንደሆነ በመቁጠር ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲኖር መደረጉ በጠቅላላው በተፈጥሮ አባት ወይም እናት እና ልጅ መካከል የሚኖሩ መብቶች በጉዲፈቻ ወላጆች እና በጉዲፈቻ ልጅ መካከልም ሳይሸራረፉ እንዲኖሩ የሚያደርግ እና ግዴታዎችንም የሚጥል እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ሁኔታ በጉዲፈቻ ልጅ እና በጉዲፈቻ አድራጊው መካከል ከሚፈጥራቸው መብቶችና ግዴታዎች ባለፈም በጉዲፈቻ ልጅየው እና የጉዲፈቻ ስምምነቱን በወቅቱ ባልተቃወሙ ከጉዲፈቻ አድራጊው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች መካከል መብቶችና ግዴታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡[12]

የጉዲፈቻ ልጅየው እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ሆኖ መቆጠሩ የሚያስገኙለት መብቶችና የሚጥልበት ግዴታዎች አሉ፡፡ የጉዲፈቻ ልጅየው እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ በመቆጠሩ ከሚያስገኙለት መብት አንዱ የጉዲፈቻ ልጅየው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከሆኑ የተፈጥሮ ልጆች ጋር እኩል በመሆን ከጉዲፈቻ አድራጊው ውርስ ሀብት ቀጥተኛ ተጠቃሚ መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 836 ሥር እንደተመለከተው የጉዲፈቻ ልጆች እንደሌሎች የተፈጥሮ ልጆች ተቆጥረው የውርስ ሀብት ተካፋይ እንደሚሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡[13] በዚህም በተፈጥሮ ልጆች እና በጉዲፈቻ ልጆች መካከል (በወራሽነትም ሆነ የእያንዳንዳቸውን ድርሻ ልክ በመወሰን ረገድ) ልዩነት ሳይደረግባቸው የጉዲፈቻ አድራጊውን የውርስ ሀብት ሊወርሱ እንደሚችሉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡[14]

የጉዲፈቻ ልጅ እንደሌሎች የተፈጥሮ ልጆች ተቆጥሮ የውርስ ሀብት ተካፋይ የመሆን መብት ተፈፃሚ የማይሆነው የጉዲፈቻ ስምምነቱን በግልጽ በተቃወሙት ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች ላይ ብቻ እንደሆነ ከተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 182 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ የጉዲፈቻ ልጅ ከሌሎች የተፈጥሮ ልጆች ጋር እኩል የውርስ ሀብት ተካፋይነት መብት በእነዚህ የጉዲፈቻ አድራጊው ዘመዶች ላይ ተፈጻሚ የማይሆነው

---

[10] መሐሪ ረዳኢ (ዶ/ር)፣ *የፌደራሉ የቤተሰብ ሕግ ይዘትና አተገባበሩ*፣ (2012)፣ ገጽ 254

[11] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 180-196

[12] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 182 (1 እና 2)

[13] የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 165፣ 1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ 19ኛ ዓመት፣ ቁ.2 አንቀጽ 836/2

[14] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 836 (1 እና 2)

የጉዲፈቻ ስምምነቱ በፍ/ቤት መፅደቁ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተቃውሟቸውን በፍ/ቤት መዝግብ ያስመዘገቡ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡[15] የጉዲፈቻ አድራጊው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች ተቃውሞ የጉዲፈቻ ስምምነቱ በፍ/ቤት መፅደቁ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍ/ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር የፀና አይሆንም፡፡ በጉዲፈቻ ስምምነቱ ላይ የፀና ተቃውሞ ከሌለ ደግሞ የጉዲፈቻ አድራጊው ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም ወደ ጎን ከሚቆጠሩ ዘመዶቹ ቀድሞ/ማ የሞተ ወይም የሞተች እንደሆነ የጉዲፈቻ ልጅየው ጉዲፈቻ አድራጊውን በመተካት ከጉዲፈቻ አድራጊው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች የውርስ ሀብት የመካፈል መብት ይኖረዋል፡፡

በዚህ ሁኔታ የጉዲፈቻ ልጅየው እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ተቆጥሮ በመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት ከጉዲፈቻ አድራጊው እንዲሁም በምትክ ወራሽነት ከጉዲፈቻ አድራጊው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች የውርስ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆን ከተደረገ በኋላ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት በተጨማሪ መውረስ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው አከራካሪው ጉዳይ የጉዲፈቻ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በሚኖረው በሕግ የተደነገገ የግንኙነት ዓይነትና መጠን ይወሰናል፡፡ ይህን ጉዳይ በቀጣዩ ርዕስ ሥር እንደሚከተለው በዝርዝር ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

## 2.2 የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

በጉዲፈቻ ስምምነት ላይ የሚደረግ ቁጥጥር ዓላማው የጉዲፈቻ ልጆችን ጥቅምና ደህንነት ማሳደግ እና ከለላ መስጠት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከተው የጉዲፈቻ ስምምነትን የሚቆጣጠረው ሕግ በተቻለ መጠን የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅም የበለጠ የሚያስጠብቅ እንዲሆን ለማድረግ ሀገራት ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ በዚህም አንዳንድ ሀገራት የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው እና ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ የሚያደርግ ሕግ ሲያወጡ ሌሎች የጉዲፈቻ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ማናቸውም ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ቅርብና ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖረው የሚያደርግ ሕግ በማውጣት የጉዲፈቻ ልጅየው ጥቅም የበለጠ እንዲጠበቅ ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡[16]

የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ የሚያደርግ ሕግ በጉዲፈቻ ልጅ እና በተፈጥሮ ወላጆች መካከል የሚኖረውን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት እስከ ማሳጣት የሚደረስ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በአንፃሩ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት እንዳለ ሆኖ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ቅርብና ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖረው የሚያደርግ ሕግ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እና የጉዲፈቻ አዲራጊዎቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብቱን በመጠበቅ ጭምር ጥቅሙን የበለጠ የሚያስጠብቅለት እንደሚሆን ይታመናል፡፡

በሀገራችንም ሕፃናትን በሚመለከት በሕግ አውጭው የሚወሰዱ እርምጃዎች ለሕፃናቱ ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጡ መሆን እንዳለባቸው ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ ተደንግጓል፡፡[17] ሕግ አውጭውም ይህን ሕገ-መንግሥታዊ ግደታውን ለመወጣት

---

[15] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 182(2)

[16] John R Jr Murphy, *supra* note 6, p. 150

[17] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 9)

የጉዲፈቻ ልጅን በተመለከተ በጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈጠር ዝምድና የጉዲፈቻ ልጅየውን መልካም አስተዳደግና ጥቅምን የሚያረጋግጥ መሆን እንዳለበት በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 194/2 ሥር ደንግጓል።[18] በዚህ ረገድ ሕግ አውጭው በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅየውን መልካም አስተዳደግና ጥቅምን ለማረጋገጥ የጉዲፈቻን ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ በመቁጠር ጥብቅ ትስስር እንዲፈጠር ከማድረግም ባለፈ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠበቀ እንዲቆይ አድርጓል።

በሌላ አነጋገር "ምንም እንኳን የጉዲፈቻ ልጅ እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ [ቢቆጠርም] ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የነበረውን ዝምድናና ትስስር ይዞ እንዲቀጥል ሕጋችን……" ስለሚፈቅድለት በዚህ ረገድ የቤተሰብ ሕጉ ከፊል የልጅነት ትስስር የሚከተል ሆኖ እናገኘዋለን።[19] ስለሆነም በጉዲፈቻ ስምምነት ዝምድና በተፈጠረ ጊዜ የጉዲፈቻ ልጅ በመርህ ደረጃ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ መቆጠሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት ይቀጥላል።[20]

ይሁን እንጂ የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ተቆጥሮ ሳለ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት የሚቀጥለው እስከምን ድረስ ነው የሚለው ነጥብ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በግልፅ ድንጋጌ እልባት አግኝቷል ለማለት አያስደፍርም። ስለሆነም የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠበቀ መቆየቱ በጉዲፈቻ ልጅየው እና በተፈጥሮ ቤተሰቦቹ መካከል ምን ምን መብቶችን እና ግደታዎችን ወይም እገዳዎችን ወይም ክልከላዎችን ጠብቆ ያቆያል የሚለው ጉዳይ በግልጽ የሕግ ሽፋን ተሰጥቶታል ለማለት አይቻልም። ይህ ማለት ግን የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት ተጠብቆ መቆየቱ ሊያጎናፅፍ የሚችለውን መብቶችና የሚያስከትለውን ግደታዎች ወይም ክልከላዎች ከተለያዩ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች በትርጉም ለማግኘትና ለማወቅ ፈፅሞ አይቻልም ማለት አይደለም።

ሆኖም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ላለው የዝምድና ግንኙነት የሕግ ጥበቃ በመደረጉ በመካከላቸው ተጠብቀው የሚቆዩትን መብቶች እና ግደታዎችን ወይም ክልከላዎችን መተንተን ሳይሆን ለጽሑፉ መነሻ ምክንያት የሆነውን በኢትዮጵያ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ መመርመር በመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ያለው ግንኙነት ተጠብቆ መቆየቱ እነርሱን የመውረስ መብቱ ላይ የሚኖረው ሚና ብቻ ተለይቶ እንደሚከተለው ይብራራል።

## 3. የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ውርስ የማግኘት መብት

ቀደም ሲል እንደተመለከተው በጥቅሉ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ያለው ግንኙነት ተጠብቆ እንደሚቆይ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቢደነገግም የዚህ ግንኙነት ተጠብቆ መቆየት የጉዲፈቻ ልጅየውን የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ ክርክር ሊነሳበት እንደሚችል ለዚህ ፅሑፍ መነሻ የሆነው ጉዳይ

18 የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 194(2)

19 መሐሪ ረዳኢ (ዶ/ር)፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ.10)፣ ገጽ 260

20 የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 183(1)

አመላካች ነው። የመከራከሪያ ሐሳቦቹም በዋናነት የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ እና ከጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ እንዲሁም የተፈጥሮ ወላጆች እና የጉዲፈቻ ወላጆች ከጉዲፈቻ ልጅየው ጋር በተያያዘ ከሚኖሯቸው መብትና ግደታዎች የሕግ ፈቃጅነት ወይም ከልካይነት ጋር ተያይዞ የሚነሱ የፍትሐዊነት ጥያቄዎችን መሠረት ያደረጉ ናቸው።

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት በሚደረግ የጉዲፈቻ ስምምነት ዝምድና ከተፈጠረ በኋላ የጉዲፈቻ ልጅየው በማናቸውም ረገድ እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ የሚቆጠር በመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ የሚኖሩት መብቶች እና ግደታዎች ወደ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ይዞራሉ። ይህም ሌሎች የመብትና ግደታ ሁኔታዎች መለወጥ እንደተጠበቁ ሆነው የጉዲፈቻ ዝምድና በመፈጠሩ ብቻ የተፈጥሮ ወላጆች ከጉዲፈቻ ልጅየው ጋር በተገናኘ የነበሯቸው ሁሉም ሕጋዊ መብቶች ከእነርሱ ተነስተው ወደ ልጅየው ጉዲፈቻ አድራጊዎች እንዲተላለፉ ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅየው የተፈጥሮ ወላጆች ከልጃቸው ጋር በተገናኘ የሚኖራቸውን መብቶች በመንፈግ ለጉዲፈቻ አድራጊዎቹ የሰጠ በመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ ንብረት አፍርቶ ቢሞት የእርሱ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉት የጉዲፈቻ ወላጆቹ እንጂ የሥጋ ወላጆቹ አይሆኑም ማለት ነው። ይህን ተከትሎ የጉዲፈቻ ልጅየውን የመውረስ መብት ለጉዲፈቻ ወላጆቹ ቅድሚያ በመስጠት የተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ከእርሱ የውርስ ሀብት እንዳይወርሱ በተደረገበት ሁኔታ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዲወርስ መፍቀድ ፍትሐዊ አይሆንም የሚል መከራከሪያ ይቀርባል።[21]

ይሁን እንጂ ይህ ዓይነት ክርክር የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው ዝምድና እንደተጠበቀ እንዲቆይ የሕግ ከለላ የተሰጠው በመሆኑ በልጅየው ቀደምት ቤተሰቦች እና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅዲሚያ የሚያሰጥ ሁኔታ እስካልተገኘ ድረስ የጉዲፈቻ ልጅ የቀደምት ቤተሰቦች የጉዲፈቻ ልጅየውን የውርስ ሀብት ሊወርሱ የሚችሉበት ዕድል እንዳለ ያላገናዘበ ነው። በዚህ ሁኔታ የጉዲፈቻ ልጅ የጉዲፈቻ አድራጊዎች እርሱን ቀድመው በመሞታቸው ምክንያት የልጅየውን የውርስ ሀብት ለመውረስ ከቀደምት ቤተሰቦቹ እና ከጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል አንዱን መምረጥ አስፈላጊ የማይሆንበት ሁኔታ ስለሚኖር የጉዲፈቻ ልጅየው የውርስ ሀብት ወራሾች የሚሆኑት የቀደምት ቤተሰቦቹ ብቻ እንደሚሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል።

ስለሆነም የጉዲፈቻ ልጅ የቀደምት ቤተሰቦች ሙሉ ለሙሉ ከልጅየው የውርስ ሀብት እንዳይወርሱ የሚያደርግ ሁኔታ በሌለበት የጉዲፈቻ ልጅ እንደጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጅ በመቆጠሩ የቀደምት ቤተሰቦቹ ከጉዲፈቻ ልጅየው ጋር በተገናኘ የነበሯቸው ሕጋዊ መብቶች ከእነርሱ ተነስተው ወደ ጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ስለተላለፉ የቀደምት ቤተሰቦች ከጉዲፈቻ ልጅየው የውርስ ሀብት እንዳይወርሱ ተደርገዋል የሚል ጥቅል ድምዳሜ ላይ መድረስ ዝርዝር የሕጉን ልዩ ሁኔታዎች ያላገናዘበ ይሆናል። በዚህ የሕጉን ልዩ ሁኔታዎች ባላገናዘበ ድምዳሜ መነሻነት የጉዲፈቻ ልጅ የቀደምት ቤተሰቦች የእርሱን የውርስ ሀብት ካልወረሱ እርሱ የእነርሱን ሀብት እንዲወርስ ሊፈቀድለት አይገባም በሚል

[21] ይህ ነጥብ ፀሐፊው የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ከሙያ አጋሮቹ ጋር ባደረገው ውይይት የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት እንዲወርስ ሊፈቀድለት አይገባም ለሚለው መከራከሪያ በምክንያትነት ይነሳ የነበረ ነው።

የሚነሳው መከራከሪያ ደግሞ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች አጠቃላይ አረዳድ መሠረት ያላደረገ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሌላው መከራከሪያ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅ ለማንኛውም ሕጋዊ ክስተትና ውጤት እንደጉዲፈቻ አድራጊው የተፈጥሮ ልጅ በመቆጠሩ[22] ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ ጉዳይ እንዲወጣው የሚጠበቅበት ግዴታ ስለሚቀርለት ግዴታው ካለባቸው ሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ፍትሐዊነት ይጎድለዋል የሚል ነው፡፡[23] በሌላ አነጋገር ክርክሩ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተገናኘ እንደሁኔታው የሚኖሩበት ቀለብ የመቁረጥ ግዴታን ጨምሮ ሌሎች ኃላፊነቶች ስለሚቀሩለት ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ የሚወጣቸው ግዴታዎች ሳይኖሩበት የእነርሱን የውርስ ሀብት እንዲወርስ ሊፈቀድለት አይገባም የሚል ነው፡፡ ለዚህ መከራከሪያ ነጥብ በዋናነት የሚነሳው ምክንያት ደግሞ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ ሊወጣቸው የሚገቡ ግዴታዎች ቀሪ የተደረጉለት የጉዲፈቻ ልጅ ግዴታዎቹ ከማይቀሩላቸው ሌሎች የተፈጥሮ ወላጆች ወራሾች ጋር እኩል የውርስ ሀብት ተካፋይ እንዲሆን መፍቀድ ፍትሐዊነት ይጎድለዋል የሚል ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የጉዲፈቻ ልጅ የጉዲፈቻ አድራጊውን የውርስ ሀብት እንዲወርስ ከተደረገ በኋላ በድጋሚ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል የውርስ ሀብት ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ በተዘዋዋሪም ቢሆን በወራሾች መካከል መድሎን የሚፈጥር በመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት ተካፋይ እንዲሆን ሊፈቀድለት አይገባም የሚል መከራከሪያም ይቀርባል፡፡[24] ሌላው ከፍትሐዊነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው መከራከሪያ የጉዲፈቻ ልጅ ሁለት ጊዜ ማለትም እንደልጅ ተቆጥሮ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹን የውርስ ሀብት እንዲወርስ ከተደረገ በኋላ በድጋሚ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዲወርስ መፍቀድ የጉዲፈቻ ልጅ ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ ስለሚሆን ይህ እንዲሆን ሊፈቀድለት አይገባም የሚል ነው፡፡[25]

ነገር ግን የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከሌሎች በሕግ ቀለብ የመስጠት ግደታ ካለባቸው ዘመዶቻቸው አንዱን መጠየቅ በማይችሉበት ጊዜ ከጉዲፈቻ ልጅየው ቀለብ የመጠየቅ መብት ያላቸው[26] በመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ ለተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ቀለብ የመቁረጥ ግደታ ሙሉ ለሙሉ ቀርቷል ሊባል አይችልም፡፡ በርግጥ የጉዲፈቻ ልጅ እንደጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ልጅ ተቆጥሮ ከእነርሱ ከሚገኙ ሁሉም መብቶች ተጠቃሚ ሲሆን ሙሉ የወላጅና ተወላጅ ግደታዎችንም የመወጣት ሕጋዊ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ከግደታዎቹ መካከል አንዱ የሆነውን ቀለብ የመቁረጥ ግደታ በሚወጣበት ጊዜ

[22] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 181

[23] ይኸኛውም ሐሳብ ፀሐፊው በጉዳዩ ላይ ከሙያ አጋሮቼ ጋር ባደረገው ውይይት የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት እንዲወርስ ሊፈቀድለት አይገባም ለሚለው መከራከሪያ በምክንያትነት የተነሳ ነው፡፡

[24] Joel B Sherman, 'Rights and Duties of the Natural Parents of an Adopted Child' (1964-1965) 20 *Intramural L Rev NYU* 142፣ ይህ የመከራከሪያ ነጥብ ፀሐፊው የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ በተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ከሙያ አጋሮቹ ጋር ባደረገው ውይይትም ተነስቶ ነበር፡፡

[25] Charles A Taylor (1967), 'Inheritance Rights of the Adopted Child in Kentucky' 55(4) *Ky LJ* 874, 878

[26] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 212(2)

በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ እና በተፈጥሮ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅድሚያ የመስጠት ግደታ[27] እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የጉዲፈቻ ልጅየው ለቀደምት ቤተሰቦቹ ያለበት ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ በቅድመ ሁኔታ የተገደበ እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉዲፈቻ ልጅ ለተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ቀለብ የመቁረጥ ግደታ ያለበት እና ይህንኑ ግደታውን ሊወጣ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ግን ከቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 212 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በቅድመ ሁኔታዎች የተገደበ ቢሆንም እንኳን የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር በተያያዘ ሊወጣው የሚገባው ቀለብ የመቁረጥ ግደታ ሊኖር እንደሚችል እየታወቀ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት ተካፋይ እንዳይሆን መከልከል ተገቢ አይሆንም፡፡

የጉዲፈቻ ልጅ የቀደምት ቤተሰቦቹን እና የጉዲፈቻ ቤተሰቦቹን (የሁለቱንም) የውርስ ሀብት እንዲወርስ መፍቀድ በወራሾች መካከል ልዩነትን መፍጠር እና የጉዲፈቻ ልጅ ያልተገባ ጥቅም ጥቅም እንዲያገኝ የሚያደርግ ስለሆነ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዲወርስ ሊፈቀድለት አይገባም የሚለው መከራከሪያም ቢሆን የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዲወርስ ቢደረግ ሌሎች ወራሾች ከድርሻቸው በላይ የሚወስዱትን የጉዲፈቻ ልጅየውን ድርሻ ከማስቀረት ባለፈ የሌሎች ወራሾችን የውርስ ሀብት ድርሻ የሚነካባቸው አይደለም፤ ይህም መሠረታዊ መብታቸውን የሚያሳጣቸው ባለመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዳይወርስ ለመከልከል የሚያበቃ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

ሌላው የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት እንዲወርስ ሊፈቀድለት አይገባም ለሚለው መከራከሪያ በምክንያትነት የሚነሳው ነጥብ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዲወርስ ማድረግ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹን የጉዲፈቻ ልጃቸውን የማጣት ስጋት ውስጥ ስለሚከታቸው ሁኔታው ልጁ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ለሚኖረው ግንኙነት እንቅፋት ሊሆን ይችላል የሚል ነው፡፡[28] ይሁን እንጂ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እንዲወርስ ማድረግ ልጁ ከጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ጋር ለሚኖረው ግንኙነት እንቅፋት ይሆናል በሚል ስጋት ብቻ እንደሚደርስ እርግጠኛ ባልሆነ ግምት የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብቱን ማሳጣት ተገቢ አይሆንም፡፡

ይልቁንም በዘመናዊ የጉዲፈቻ ስምምነት አረዳድ የጉዲፈቻ ዓላማ የሆነውን የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅምና ደህንነት የበለጠ ማስጠበቅ የሚችለውን የሕግ አተረጓጎም በመከተል ለጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብቱን ማረጋገጥ የሕጉን መንፈስ የተከተለ አረዳድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት በተመለከተ ግልፅ ድንጋጌ ባለመኖሩ ፍ/ቤቶች ስለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የቤተሰብ ሕጉን ድንጋጌዎች ሲተረጉሙ የጉዲፈቻን ዓላማ ሊከተሉ ይገባል፡፡ ይህም የጉዲፈቻን ዓላማ መሠረት ያደረገ አተረጓጎም፣ የጉዲፈቻ ልጅየውን ጥቅምና ደህንነት የበለጠ ማስጠበቅ የሚችለውን አማራጭ በመከተል፣ ለጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብቱን በሚያጎናፅፍ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ከተቆጠረ በኋላ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹም ጋር ያለው የዝምድና

---

[27] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 183(3)

[28] Paul A Kiefer, *supra* note 1, p. 395

ግንኙነት እንዲቀጥል መደረጉ[29] ሕጉ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹ እና የጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ (የሁለቱም) ልጅ እንዲሆን እንዳደረገው ለመገንዘብ ይቻላል። በዚሁ አግባብ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹ እና የጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ (የሁለቱም) ልጅ እንዲሆን መደረጉ ከሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶችና ክስተቶች መካከል የጉዲፈቻ ልጅየው የውርስ መብት አንዱ[30] ሲሆን ይህም የሁለቱንም (የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እና የጉዲፈቻ አዲራጊዎቹን) የውርስ ሀብት የመውረስ መብት የሚያጎናጽፈው ነው። ይህ ሆኖ ሳለ በወራሾች እና ተወራሾች እንዲሁም በወራሾች በራሳቸው መካከል ከሚኖር መብትና ግደታ አኳያ በተቃኘ የመብትና ሀብት ልዩነት መነሻነት በሚነሳ የፍትሐዊነት ጥያቄ ብቻ የጉዲፈቻ ልጅ የጉዲፈቻ አዲራጊውን እና ቤተ-ዘመዶቹን የውርስ ሀብት ብቻ እንጂ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን እና ቤተ-ዘመዶቻቸውን የውርስ ሀብት እንዳይወርስ መከልከል አሳማኝ አይደለም።

የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ግልፅ የሆነ የሕግ ድንጋጌ አለመኖሩም ቢሆን ሕግ አውጭው የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት እንዳይኖረው የማድረግ ሐሳብ እንዳለው ግምት የሚያስወስድ ሁኔታ በሌለበት ይህንን መብቱን የሚነፍግ የሕግ ትርጉም መከተል የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘ አረዳድ ይሆናል። የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት እንዳይወርስ በግልጽ አልደነገገም። ይልቁንም ሕጉ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ጋር ጥብቅ ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖረው ካደረገ በኋላ ከተፈጥሮ ቤተ-ዘመዶቹም ጋር የነበረው ቤተሰባዊ ትስስርም እንደተጠበቀ እንዲቆይ በማድረጉና የልጁን መብትና ጥቅም ይበልጥ ሊያስጠብቅ የሚችለውን አካሄድ በመከተሉ፣ ሕግ አውጭው የተጣለትን ለሕፃናት ደህንነት ቅድሚያ የመስጠት ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ ተወጥቷል ሊባል ይችላል።

የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በጠቅላላ እንደተጠበቀ የሚቆይ ሆኖ ሳለ እና የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት ሊወርስ አይችልም የሚል ግልጽ የሕግ ክልከላ በሌለበት ሁኔታ፣ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት የሚያሳጣ የሕግ አተረጓጎም ስልት መከተል ከቤተሰብ ሕጉ አረዳድ የወጣ ይሆናል። ስለሆነም፣ በሕግ በግልጽ እስካልተደነገገ ድረስ በጉዲፈቻ ልጅ እና በተፈጥሮ ቤተሰቦቹ መካከል ያለው ዝምድና ተጠብቆ እንዲቆይ መደረጉ በራሱ የጉዲፈቻ ልጅየው ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት ተካፋይ የሚያደርገው ሆኖ ሳለ በጉዲፈቻ ስምምነቱ ምክንያት ብቻ ይህ የውርስ መብት ሊነጠቅ የሚችልበት አግባብ አይኖርም።

በተጨማሪም የጉዲፈቻ ልጅ የጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ሀብት ሳያፈሩ ሊሞቱ ወይም ሊረዱት የማይችሉ ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር ስለሚችል የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት እንዳይኖረው የሚያደርግ ግልጽ የሕግ ክልከላ በሌለበት እንደዚህ ያለውን ንፁህ እና ረዳት የሌለውን የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብት የሚያሳጣ አካሄድ መከተል ፍትሐዊ አይሆንም።[31] በሌላ አነጋገር በጉዲፈቻ ልጅ እና በተፈጥሮ ቤተሰቦቹ መካከል የሚኖር ትስስር እንዲቀጥል የሚያደርገው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌ ንፁሃን እና ረዳት የሌላቸውን የጉዲፈቻ

[29] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ (ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3)፣ አንቀጽ 181 እና 183(1)

[30] John R Jr Murphy, *supra* note 6, p. 150

[31] Paul A Kiefer, *supra* note 1, p. 398

ልጆች የተፈጥሮ ወላጆቻቸውን የመውረስ መብት በሚያሳጣ መልኩ በጠባቡ ሊተረጎም አይገባም፡፡

ስለሆነም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የጉዲፈቻ ስምምነትን ለመግዛት በተቀመጡ ድንጋጌዎች የትኛውም ቦታ ላይ ግልጽ ክልከላ ባልተቀመጠበት ሁኔታ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብቱን ሊነጠቅ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ማለትም፣ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የመውረስ መብቱ በሕግ አውጭው በግልጽ እስካልተደነገገ ድረስ ፍ/ቤቶች የዝምድና ሐረግን መሠረት በማድረግ የውርስ ሀብቱ ተካፋይ እንዲሆን መፍቀድ ይኖርባቸዋል፡፡[32] በዚህ አግባብ የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ወላጆች ያለኑዛዜ በሞቱ ጊዜ የጉዲፈቻ ልጅየው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆን የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት ለመውረስ ወይም የውርስ ሀብቱ ተካፋይ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 4. መደምደሚያ

የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ወይም ቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት የሚወሰነው የጉዲፈቻ ስምምነትን እና ሥርዓትን በሚገዛው የጉዲፈቻ ሕግ እንደሆነ በዚህ ጽሑፍ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በአንድ አገር የጉዲፈቻ ስምምነትን እና ሥርዓትን ለመግዛት በሚወጣ ሕግ መሠረት፣ የጉዲፈቻ ልጅ ፍፁም እንደጉዲፈቻ አዲራጊዎቹ ልጅ እንዲቆጠር እና ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ እንዲቋረጥ ሊደረግ ይችላል፡፡ በአንፃሩ የጉዲፈቻ ልጅ እንደጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ልጅ ተቆጥሮ ጥብቅ ትስስር እንዲኖረው የማድረጉ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነትም ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያደርግ የጉዲፈቻ ሕግና ሥርዓት ሊዘረጋ የሚችልበት ሁኔታም ሊኖር እንደሚችል ከተለያዩ ሀገራት የጉዲፈቻ ሕግ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለጉዲፈቻ ስምምነት እና ሥርዓት የሚደነግገው የኢትዮጵያ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ጋር ጥብቅ ትስስር እንዲኖረው ከማስቻሉም በላይ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነትም ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያደርግ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር የሚኖረው ዝምድና ተጠብቆ እንዲቆይ የሕግ ጥበቃ የተደረገለት መሆኑ ከሚያስገኝለት መብቶች መካከል ደግሞ የውርስ መብት አንዱ ነው፡፡ በዚህም የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ጋር በሚኖረው ግንኙነት እንደልጅ የሚያገኛቸው ማናቸውም ዓይነት መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን የውርስ ሀብት የመውረስ መብት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፣ የጉዲፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ የውርስ ሀብት ተካፋይ እንደይሆን የሚያደርግ ግልጽ የሆነ የሕግ ክልከላ የሌለ መሆኑንና ይህ የውርስ መብቱ የሚነፈግበት የሕግ አግባብ እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ■

---

[32] John R Jr Murphy, *supra* note 6, p. 152

## የተጠቀሱ ጽሑፎች (Cited References)

መሐሪ ረዳኢ (ዶ/ር) (2012 ዓ.ም)፣ *የፌደራሉ የቤተሰብ ሕግ ይዘትና አተገባበሩ*

Bjertness, Donald (1957). 'Domestic Relations - Inheritance by Adopted Children - Right of Adopted Child to Inherit from Its Natural Parent' 33(2) *N.D. L. Rev.*

Kiefer, Paul (1966). 'Intestate Succession, Sociology and the Adopted Child', 11(2) *Vill L Rev*

Murphy, John (1957). 'Adopted Child's Right of Inheritance from the Natural Parents', 6 *Clev-Marshall L Rev*

Sherman, Joel, 'Rights and Duties of the Natural Parents of an Adopted Child' (1964-1965), 20 *Intramural L Rev NYU*

Taylor, Charles (1967). 'Inheritance Rights of the Adopted Child in Kentucky', 55(4) *Ky LJ* 874

Thompson, Arthur (1917). 'Right of the Adopted Child in Intestate Succession', 3(2) *ABA J* 135